# ስንፈተ መንግስት - ድርቅ፣ ብጥብጥና ኤርትራ

ዳደ ደስታ

ድርቁም ብጥብጡም አጋጥመው ባይሆን ጥሩ ነበር። ካጋጠሙ አይቀር ግን መንግስት ወሳኝ ስራዎች ለመስራት ይጠቀምበታል የሚል ተስፋ አለኝ። "ከባባድ ቀውሶችን በከንቱ ማባከን አይገባም" ብለው የተናገሩት አሁን የቺካጎ ከንቲባ ራም ኢማኑኤል ናቸው። እሳቸው ይህን ሲሉ አደገኛ ፖሊቲካዊ ቀውሶች ብዙውን ጊዜ እንደመዘዝ ይታያሉ እንጂ በደህና ጊዜ መፍታት ያቀተን ውስብስብ ችግር ለአንዴና ለመጨረሻ መፍትሄ ሰጥቶ ለመሻገር ልዩ ዕድል ይዘው እንደሚመጡም ልብ ማለት ያስፈልጋል፣ ማለታቸው ነው። የጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማርያም መንግስትና ኢህአዴግ አሁን በኦሮምያና በጥቂቱም በጎንደር አካባቢ የታዩ አውዳሚ ህውከቶች ያለምክንያት የተፈጠሩ አንዳልሆኑ መገንዘብ አለባቸው። ይህ መቼም ክርክር የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም። ህይወትና ንብረት የተገበረባቸው አመጾች በመሆናቸው የሚፈለጉና "እንኳንም ተፈጠሩ" የሚሰኙ አይሆኑም። መፈጠራቸው ካልቀረ ግን እነሱንና ሌሎች ብዙ ልዩ ልዩ አጥፊ ችግሮች ለመቀፍቀፍ ምክንያት እየሆኑ ያሉት ፖለቲካዊና አስተዳድራዊ ሁኔታዎች ለመቀየር ቁርጠኛ ስራ ለመስራት በከፍተኛ ዋጋ የተገኙ ማንቂያ ደወሎች እንደሆኑ መገንዘብ ግድ ይላል።

ድርቁና ውጤቱም ሁሌ ከሰማይ የሚወርድ ተፍጥራዊ እርግማን ተደርጎ በዝናብ እጥረትና ለምግብ እጥረት ተጋላጭነት መካከል፣ ለምግብ እጥረት በመጋለጥና በረሃብ መጠቃት መካከል ድንበር የሌለ ያህል አንዱ ጠንቅ፣ ሌላኛው አይቀሬ ውጤት አድረገን ከማሰብ ባህል መውጣት አለብን። በአሁኑ ጊዜ፣ ኢትዮጵያ በከፍተኛ የልማት ጉዞና የገጽታ ግንባታ ላይ ባለችበት ምዕራፍ፣ ድርቁ ያለ ውጭ እርዳታ ልመና ልንቋቋመው ያለመቻላችንም የመልካም አስተዳደር ችግር መገለጫ ነው። እንግዲህ ግንባሩና መንግስቱ 'መልካም አስተዳደር ማስፈን ዋናው የሞት የሽረት ተልዕኮዬ ይሆናል' ብለዋል። የችግሮቹ ማሳያዎቹም ይኸውና ቁልጭ ብለው ይታያሉ። የጠ/ሚ/ር ኃ/ማርያም መንግስትና ኢህአዴግ እነዚህ ሁለት ዓበይት ሁኔታዎች (ቀውሶች) የመልካም አስተዳደር እጦት የፈጠራቸው እንደሆኑ ተገንዝበ፣ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት እንደ ወሳኝ መታገያ ማተርያል ሊጠቀምባቸው ይገባል። እንዲህ ያለውን አጋጣሚ በከንቱ መባከን የማይኖርበትም ለዚህ ነው።

## ጆፌ አሞራዎች!

ሌላኛው ዓቢይ ከስተት አመጹና ህውከቱ ነው። ሻዕቢያና የሻዕቢያ ደጋፊዎች የጎሞጁለት ፌስታ መሆኑ የሚገርም የለውም። ድንክ ተንታኞቹም፣ ጎምቱ ምሁራንም፣ የከንቲባነት ምኞት ያሰከራቸውም ሌሎቹም። ከዛ ይልቅ በኤፌኮ፣ በመድረክ፣ በሰማያዊ ፓርቲ፣ በኢሳት፣ በግንቦት 7፣ በኦነግ፣ በነፕሮፌሰር መሳይ ከበደና በነጃዋር መሓመድ ወዘተ በመሳሰሉት ተሰፈኞች የተስተዋለው መጎምጀትና ጆፌ አሞራነት ከግርምት በላይ የሚገርም ነው። መንግስት "የህዝብን ጥያቄ ሰምቶ ተገቢ ማብራርያና ምላሽ ይስጥ፣ የዜጎች መብት ያክብርና ያስከብር፣ ህግና ሰላም አይፍረሱና አይደፍርሱ" የሚል ሳይሆን በአንድ በኩል ህውከቱም ውድመትም ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ህግና ስርዓት ለማስጠበቅ የሚደረጉ ጥረቶችን ለማማበባሻነትና ለመቀስቀሻነት በመጠቀም የሲኦል ምድር አዋጅ ነጋሪት ሲጎስሙ ማየት እጅግ አሳዛኝና አብጋኝ ነበር።

ለምሳሌ የሰማያዊ ፓርቲ እንደሸማኔ መወርወርያ ለዓይን እይታ በሚያዳግት ፍጥነት ከአንድነትና አሃዳዊነት ዘማሪነት ወደ ድምጻችን ይሰማ የሃይማኖት ጎራ፣ ቆይቶም "ኢትዮጵያ የነቃሽ፣ አራሽና ተኳሽ አገር ትሆናለች" ከሚለው ማኒፌስቶው ተላቆ ከመቼው የኦሮሞ ህዝብ ህገመንግስታዊ መብቶች ተቆርቋሪ ወደመሆን እንደተሸጋገረ ይገርማል። ህገ መንግስቱና መንግስታዊ ስርዓቱ ለብሄር ብሄረሰቦች መብት የተለጠጠ እውቅናና መብት መስጠቱ

“ለአገር አንድነትና ለአገር ህልውና አደገኛ ነው” የሚል ፖለቲካዊ መነሻ ያላቸው ኃይሎች በምን ዓይነት ቅዱስ ጋብቻ “የኦሮሞ ህዝብ ህገመንግስታዊ መብት ተጥሷል” ከሚሉ ኃይሎች መቀናጆ እንደፈጠሩ የሚገባን የፖለቲካ ጅብነታቸው ስንገነዘብ ነው። እንደሚታወቀው ጅብ ርሃቡን ለማስታገስ ሁለገብ ስልት ይጠቀማል። እስከሚነክስም ያነክሳል። የሚጸየፈው አጀንዳና ተግባር የለውም። ሌላ ከጠፋ የቆሻሻ ክምር ይፈትሻል። ከቸገረው ጓደኛውን ይበላል። ርሃቡና ሆድ ወዳድነቱ የራሱን ቁስል ለምግብነት እስከመከጀል ያደርሷል። የስልጣን ርሃብም ከማይመስልህ ኃይል ጋር ያሰልፋል። አገርህን ሊያጠፋ ለተሰለፈ ጠላትም በተላላኪነት ያሳድራል። ይህ እውነትም ፖለቲካዊ ጅብነት ነው። የነዚህ ኃይሎችና ግለሰቦች ጸያፍና አሳፋሪ እንቅስቃሴ ለታሪክ ተሰንዶ መቀምጥ አለበት። ወደፊት እንደጤናማ ሰዎች ለምርጫና መሰል ጉዳዮች ህብረተሰብ ፊት ለመቅረብ በሚፈልጉበት ጊዜ ይህ ተግባራቸው እየተመዘዘ ሊነገርባቸው ይገባል። የመንግስት ስንፈትና አስተዳደራዊ ችግር ሌላ ጉዳይ ሆኖ የነዚህን ድንክ የፖለቲካ ጥንብ አንሳዎች አፍራሽ ስራ ፈጽሞ የሚረሳ አይሆንም። ነገር ግን ከነዚህ ኃይሎች ጨዋነትና ለአገር የሚቆረቆር ኃላፊነት የሚጠብቅ የዋህ የለም። ያው ከግርግሩ በኃላ አድፍጠው ይቆያሉ። እንደገና ኮሽታ ሲሰሙ አባሯቸውን አራግፈው ከነብልግናቸው ብቅ ይላሉ። የኛ ጉዳይ የመንግስት ሥልጣንና የማስተዳደር ኃላፊነት ከወሰደው አካል ጋር መሆን አለበት።

## ስንፈተ መንግስት የፈጠረው ህውከት!

የጎንደሩ ዓመጽ መነሻ ምክንያቱም ስፋቱም ከኦሮምያው አነስ ያለም ቢሆንም፣ ወይም ደግሞ አንዱ የመሬት ሌላው የምሬት መስለው ቢታዩም፣ በአነሳሳቸውም በውጤታቸውም ሁለቱም ይመሳሰላሉ። ስለዚህ የኦሮምያን ህውከት በማየት ሁለቱንም እናያለን። ሁሉም በዚህ ዓይነት የሚከሰቱ ህውከቶች የሚነሱበት ሰበብ አላቸው። ሁሉም ግን ዋናው ጉዳያቸው ሰበብ አድርገው የተነሱበት ጉዳይ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ለምሳሌ በዚሁ ወቅት መነሻ ሰበብ የሆነው የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ነው። ማስተር ፕላኑ በይዘት ደረጃ ጥሩ ነው አይደለም የሚለውን ክርክር ለጊዜው አቆይተን፣ ለምን አሁን ህውከት ለመቀስቀስ ምክንያት ሆነ የሚለውን ለመመለስ እንሞክር። ማስተር ፕላኑ በመንግስት ባለሙያዎቹ ተዘጋጅቶ ወደ ትግበራ ለመሸጋገር የሚቀሩት ብዙ ምዕራፎች አሉ። ለምሳሌ ገና ህዝብ አልተወያየበትም። እንደህግና ፖሊሲም ገና መጽደቅ ያለበት ነው። ለዛ ደግሞ የሚመለከታቸው የአዲስ አበባና የኦሮምያ ም/ቤቶች በየራሳቸውና ምናልባትም በጥምረት ሊመካከሩበት የሚጠበቅ ነገር ነው። ከዚህ ሁሉ በፊት፣ ቴክኖክራት ባለሙያዎች እንዳዘጋጁት በቀጥታ ህግ ሆኖ ወደ ትግበራ ይሄዳል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው።

በሌላ በኩል ግን “ይህ ማስተር ፕላን የኦሮምያን መብት ደፍጥጦ ወደ ተግባር እየተሸጋገረ ነው” በማለት ሆን ብለው የሚቀሰቅሱ ያሉ ያህል የሚቀበላቸውና የሚቀሰቀስላቸው ማህበረሰብም አለ። መንግስት ዘግይቶም ቢሆን ወሬውን ለማስተባበል ቢፈልግም ሊሰሙት ያልፈለጉት ወይም ያላመኑት የህብረተሰብ ክፍሎች አሉ። በዚህ ላይ “አይዟቹህ፣ ግፉ፣ አጠናክሩ” ብለው ከርቀትና በሶሻል ሚድያዎች ነገሩን ለሚያፋፍሙ ሰዎች ጆሮ ሰጥተው ወደ ዓመጹ ተቀላቅለው ለመጉዳትም ለመጎዳትም ተዘጋጅተውና ወስነው የዓመጹ አካል ሆነው ለመቀጠል የፈለጉ ዜጎች ነበሩ ማለት ነው። እነዚህም ንብረቶችን እሰካማውደም፣ የጸጥታ ሃይሎችን እሰከመጋፈጥ ደረሱ። ጎጂዎችም ተጎጂዎቹም የታዩበት አሳዛኝና አውዳሚ ክስተት ሆኖ ቀጠለ። በዚህ ዓመጽ ተሳታፊ የነበሩ ወገኖች፣ ተግባር ላይ ለመዋል ብዙ መንገድ የቀረውን ማስተር ፕላን ልክ ተግባር ላይ እንደዋለ፣ ሌሎች አጋጋዮች ከርቀትና ከቅርብ የሚሉትን እንደ እውነት፣ የፈደራል መንግስትና የኦሮምያ ባለስልጣናት የሚሰጡትን ማብራርያን ያለማመን፣ ከዚያም የህዝብና የግለሰብ ንብረቶችን እስከማውደምና የጸጥታ ሃይሎችን እስከመጋፈጥና መገዳደል የደረሱበት ሁኔታ ሲታይ እንቆቁልሹ የሚፈታልን ምንጩ የመልካም አስተዳደር ዴፊሲት መሆኑን ነው። መንግስትና መስተዳድሩ በወቅቱ መረጃዎች አለማድረስና የሚመለከተውን ማህበረሰብ የሂደቱም የፕላኑም አካል አድርጎ አለማሳተፉ የፈጠረው

ክፍተት ነው። ይህም የግልጽነትና የአሳታፊነት ችግር በመንግስት ደረጃ ሲሆን ፖሊቲካዊ ስም አለው። የመልካም መስተዳድር ጉድለት ነው።

የመልካም መስተዳድር ችግሩ ህውከቱ እንዲፈጠር ማድረጉ ብቻ ሳይሆን ከተፈጠረ በኋላ በነበረው አያያዝም የታየ ነው። በሰለጠነው ዓለም ህይወት ይቅርና ንብረት ለወደመበት ክስተት ፓርላማዎቹና አስፈጻሚ አካል ውስጥ የመጨረሻውን የስልጣን እርከን የያዙ መሪዎች ከክልሉ ባለስልጣናት በቅንጅት ሃላፊነት ወስደው ማብራርያ ይሰጡበታል፣ በፖለቲካዊ መልኩ የሚለይ የችግሩ ተጠያቂ አሳውቀው፣ በህጋዊ መልኩ የሚጠየቀው ለህጉ ትተው፣ የማስተካከያና የእርምት እርምጃ ወስደው ያረጋጋሉ። ይህ በኛ አገር በኦሮምያ ያጋጠመው ጉዳይ ስናይ ግን ገና የአካባቢው ባለስልጣናት መፍታት እስኪያቅታቸው ድረስ፣ የክልሉ መስተዳድር ከአቅም በላይ እስኪሆንበት ተጠብቆ ከረፈደና የተወሳሰበ አቅጣጫ ከያዘ በኋላ ነው የሚገባው። ይህም አስተዳደሩ ሩቅ ወይም ግድ የለሽ አለዘም ሁኔታዎች በፍጥነት ገምግሞ የመፍትሄው ባለቤት ለመሆን የብቃት ማነስ ያሳያል።

ፓርላማው በነዚህ ጉዳዮች ሲነጋገርና የሚመለከታቸው ሃላፊዎችን እየጠራ በጥያቄ ሲያፋጥጥ፣ ከባለሙያዎችና እውቀተኞች ስለጉዳዩ ጥልቅ ማብራርያ ሲያዳምጥ፣ የህግና የፖሊሲ ምላሽ በሚጠይቁ ክፍተቶች አዋጆችና ረቂቅ ህጎች ሲጽፍ ስራ በዝቶበት አናየውም። የላይኛው ቤት የሚባለው የፈደሬሽን ምክር ቤትም ለአዲሱ የፓርላማ 5 ዓመት ዘመኑ መክፈቻ ስነስርዓት ከተሰየመ በኋላ በምን ሥራ እንደተጠመደ አናውቅም። ለምሳሌ ለኦሮምያው ብጥብጥ ሰበብ የሆነው የአዲስ አበባውና ኩታ ገጠም የኦሮምያ ከተሞች ማስተር ፕላን ሁለት ክልሎችን የሚነካ አጀንዳ ነው። እንዲህ ዓይነት ክልል ዘለል የሆነ አጨቃጫቂ ጉዳይ ሲኖር ፌዴሬሽን ምክር ቤቱ መፍትሄ እንዲሰጥ ህገ መንግስቱ ስልጣንና ኃላፊነት የሚሰጠው ለዚሁ ም/ቤት ነው። እንደውም አንዱ ክልል ወይም ክልሎች ህገመንግስታዊ ስርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሲፈጥሩ ፈደራል መንግስት ጣልቃ እንዲገባ እሚያዝዘው ይኸኛው ም/ቤት ነው። በዚህ ላይ ህገመንግስቱን የመተርጎም ስልጣንም የዚህ ም/ቤት ስልጣን መሆኑ ያታወቃል። ለምሳሌ ህገመንግስቱ ኦሮምያ በአዲስ አበባ ላይ ልዩ አስተዳደራዊ ጥቅሟ ይጠበቅባታል በሚል በህገመንግስቱ ላይ የሰፈረው ድንጋጌ መንፈስም ይዘትም የመተንተን ኃላፊነት ለዚህ ም/ቤት የሚቀርብ ስራ ነው። በዚህ ላይ የችግሩ ሰበብ "የኦሮምያ ህገመንግስታዊ መብት ተጥሷል" የሚል በመሆኑ የዚህ ዓይነት ህገመንግስታዊ መብት ጉዳዮች ሲነሱ በሙሉ ስልጣን መናገር ያለበት አካል ሆኖ ሳለ ስራ ላይ የሌለ እስኪመስለን ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ውስጥ አይስተዋልም።

### ኢትዮጵያን እያስተዳደረ ያለው ኤልኒኞ አይደለም- ኢህአዴግ ነው!

በእርግጥ የድርቁ መንስኤ ኤልኒኞ ነው። በድርቁ ምክንያት የተፈጠረው የምግብ አቅርቦት እጥረት ቀውስ ግን ፖሊሲ-ወለድና አስተዳደራዊ ነው። እርግጥ በኢትዮጵያ ታሪክ "ታላላቅ ድርቆች" እየተባሉ ከሚጠቀሱት መጠነ-ሰፊ ድርቆች ያልተናነሰ ሆኖ ሳለ እንኳን ከትልልቆቹ ረሃቦች ከአነስተኞቹም የሚመጣጠን አይነት ጉዳት- በተለይም በሰው ህይወት ላይ- እስከአሁን ስላላየን የምንጽናና ዜጎች አንጠፋም። ይህ ግን ልክ አይሆንም። መንግስት "የስንዴ እርዳታ መጠየቅ እንደ ፈረንጆቹ በ2015 እናቆማለን" የሚል በይፋ ያልታወጀ ውሳኔ ወስዶ እንደነበር ይታወቃል። ይህ ማለት መቸም "ኤልኒኞ ፊቱ ወደኛ እንዳያዞር ስምምነት ተፈራርመናል" ማለት ሊሆን አይችልም። ትርጉም እሚኖረው፣ 'በማንኛውም ምክንያትና የዝናብ እጥረት ሊያጋጥም እሚችለውን ችግር ለመቋቋም የሚያስችል ፖሊሲ፣ መዋቅር፣ አሰራርና ተፈላጊ ዓቅም ፈጥረናል' ማለት ሲሆን ብቻ ነው። መጀመርያ "የስንዴ እርዳታ እሰከመጨረሻ አስቀራለሁ፣ ቆይቶ ደግሞ "ይሄኛውን ድርቅ በራሴ ዓቅም እወጠዋለሁ"፣ ኋላ ላይ "የዓለም እገዛ ያስፈልገናል" በሚሉ ቁልቁል እየተንሸራተቱ የሚሄዱና ለዓለም አቀፍ ሚድያዎች የማያባራ ዜናዊ ግብአት በሚሆን መልኩ አገራዊ ኩራታችን

በችርቻሮ እየተሽረሸረ እንዲሄድ የሆነበት ምክንያት ዝርክርክነት እንጂ የግድ ስለነበር አይደለም። ቁጥሮችም መቋጠርያ አጥተዋል። ለ4.5 ሚልዮን ተረጂዎች፣ የለም ለ8.2፣ የለም ለ10.2 እየተባልን እዚህ ደረስን። ቀጥሎ ወረፋ ላይ ያለው ቁጥር ደግሞ 15 ሚልዮን ነው..!

ድርቁ ላይ አንድ ሁለት ነጥቦች አክዬ ወደ ሰሙኑ ህውከት እመለሰላሁ። አንድ ችግር ደጋግሞ ስለመጣ እና እስከአሁን ሳይፈታ ስለቀጠለ መፍትሄውም ያን ያህል ውስብስብ መሆን አለበት ማለት አይደለም። ለምሳሌ እስከተቻለ ድረስ ትላልቅና አነስተኛ የመስኖ እርሻዎችን ማስፋፋት፣ የውሃ ማቆር ስራዎችን በያንዳንዱ ቤት እንዲተገበር ማስተባበር፣ የእርሻ ምርቶችና ጥሪቶችና ሃብቶችን የድርቅ፣ በሽታና ያልታሰበ ውድመት ኢንሽራንስ አገልግሎት መዘርጋት፣ ይህ ዓቅም የሚጠይቅና በቅርብ ሊተገበር የማይችል ከሆነ ደግሞ የሰው ምግብና የእንስሳት መኖ ኢንሹራንስ በገጠር መዘርጋት፣ መንግስት አሁን እየሰራው ያለውን ስትራተጂክ የምግብ እህሎች መጠባበቂያ ክምችት መጠን ማሳደግ፣ የምግብ እህል ቁጠባ፣ ማለትም በደህና ምርት ጊዜ ገበሬዎች የሚያስገቡት ትርፍ ምርት መንግስት ልክ ባንኮች ጥሬ ገንዘብን ወለድ እየከፈሉ እንደሚያስቀምጡት መንግስትም ትርፉን ምርት ከገበሬዎች እየተረከበ በገንዝብ ወይም ራሱ ያስቀመጡትን እህል በወለድ እያስቀመጠ በፈለጉት ጊዜ ወለዱን (በገንዘብ ወይም በጥሬ እህል) ጨምሮ መመለስ፣ ወዘት፣ እነዚህን ልዩ ልዩ መፍትሄዎች በማቀናጀት ስራ ላይ ማዋል ይቻላል። በነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የማይሸፈኑ ገበሬዎችና የከተማ ድሃ ነዋሪዎችን መንግስት በጀት መድቦ ከራሱ ካዝና ወይም ወይም በፈቃደኝነት ለዚህ ዓላማ ከሚያዋጡ በጎ አድራጊ ዜጎች እያስተባበረ መደጎም ይችላል። ዋናው ነጥብ ዜጎች የሚበሉት ምግብ ማጣት የለባቸውም። ምግብ ላጡት ዜጎች መሰራታዊ መብት ነው፣ እንደ ሃገርና ማህበረሰብ ደግሞ ዜጎች ምግብ እንዳያጡ መንከባከብ ወገናዊ ግዴታ ነው። መንግስት ግን በሃላፊነት የተቀበለው ከዋና ስራዎቹ አንዱ እንደሆነ ይታወቃል።

ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትና የገዢው ፓርቲ ሃላፊዎች ድርቁን በተመለከተ ከሚሰጡዋቸው ማብራርያዎች ዋናውን ጉዳይ ትተው ሌሎች ፈጽሞ የማይመጥኑና የማያስፈልጉ ነጥቦች ሲያነሱ ይደመጣሉ። ለምሳሌ "ድርቁ ኤልኒኞ ያመጣው ጣጣ ስለሆነ በኛ አገር ላይ ብቻ የተከሰተ አይደለም፣ በካሊፎርንያም በአውስትራሊያም ነው" የሚለው ምላሽ አንዱ ነው። ይህ ግን ምላሽ እሚሆነው "ከኛ ውጭ ኤልኒኞ ድርቅ ያስከተለባቸው ሌሎች የዓለማችን ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?" ተብሎ ሲጠየቅ ብቻ ነው። አለዛ ካሊፎርንያና አውስትራሊያ በምግብ እጥረትና የረሃብ አደጋ ሲቸገሩ አልታየም። እነዚህ በድርቅ ተነክቷል ተብለው በኛ ባለስልጣናት ከሚጠቀሱት አካባቢዎች የሚመለከተን ጉዳይ ቢኖር እንደኛው የድርቅ ሰለባ ሆነው ሳለ፣ ዜጎቻቸው ለምግብ እጥረትና ለስንዴ እርዳታ ያልተጋለጡበት ሚስጥር መርምሮ ማግኘት ነው። እምብዛም የሚያመራምር ሚስጥር ግን አይደለም። ትክክለኛ ፖሊሲ፣ መዋቅር፣ አሰራርና ዓቅም በትክክለኛው ጊዜና ቦታ አስቀምጦ መገኘት ነው። ይህ በሌላው ስሙ መልካም አስተዳደር እሚባለው ነው። ሌላው፣ በፍጹም በፍጹም መባል ያልነብረበት ግን በባለስልጣኖቻችን አንደበት አልፎ አልፎ ሲባል እምንሰማው ለምግብ እጥረት የተጋለጠው የዜጎች ቁጥር ወደ መቶኛ ማነጻጸርያ በመለወጥ ከ90 ሚልዮን ህዝብ 80 ሚልዮን ህዝብ ለምግብ እጥረት አልተጋለጠም፣ በመቶኛ ሲሰላ "ከዚህ በፊት ከተከሰቱ ረሃቦች በተሻለ ሁኔታ እንገኛለን" የሚለውን ነው። ጉዳዩ ግን "ስንት ኢትዮጵያውያን ሆዶች ተርበው አደሩ" በሚል ሰብአዊ ሃላፊነት በሙሉ ዓቅም የሚጋፈጡት እንጂ "ከስንት ስንት" በሚል ስታቲስታካዊ ንፅፅር የሚያመልጡት አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ 50 ሚልዮን እያለ የሚራቡ 5 ሚልዮን ዜጎችና አሁን 90 ሚልዮን ከደረስን በኋላ የሚራቡ 5 ሚልዮን ዜጎች በቁጥርም በሰብአዊ ሚዛንም አይበላለጡም። 50 ሚልዮን እያለን የሚሞት አንድ ሰውና 90 ሚልዮን ከደርስን በኋላ የሚሞት አንድ ሰው፣ በህልውናም፣ በፍጥረታዊ ዋጋም እኩል ናቸው። ቁጥሮችን በመቶኛ ማነጻጸር ተገቢነቱ ለቁጥሮች እንጂ ለሰዎች አይደለም። አስተሳሰቡም ሰብአዊ ሳይሆን ማተማቲካል ነው። ይህ

መተው ያለበት አቀራረብ ነው። የመልካም አስተዳደር መርህ አንድም ዜጋ በችጋር መጎዳት የለበትም፣ የሚል እንጂ ከመቶ ስንት አገኘሁ፣ የሚል ሆኖ አያውቅም።

## በኤርትራ ጉዳይ ላይ!

የኢትዮጵያ መንግስት የኤርትራን ጉዳይ የኢትዮጵያን ስትራተጂክ ጥቅም አካል አድርጎ የመያዝ አስፈላጊነቱ በግልጽ እያየን ነው። አሁን እንደሚታየው ለአንድ ሴኩሪቲ ፖርቶፎልዮ ወርውሮ መቀመጡ በኢትዮጵያ ላይ እየፈጠረው ያለውን ጂኦፖለቲካል ተጋላጭነት አስረጅ አያስፈልገውም። አንደኛ የኤርትራ መንግስት ፖለቲካዊ መርህም፣ የኤርትራ ገዢ ጥቅም የማስጠበቅ ሃላፊነትም የማይገዙት ኃይል ሆኖ የዘለቀ ይመስላል። ኢትዮጵያን ሊጎዱ የሚፈልጉ ኃይሎች በተላላኪነት እንዲያሰሩት ራሱን አዘጋጅቶ የተቀመጠ መንግስት ነው። እሱን እንዲላኩት የመለመላቸው ከኢትዮጵያ በጥገኝነት ኤርትራ ውስጥ የሚገኙት ቡድኖችም ለእንደዚህ ዓይነት ተግባር በተጠንቀቅ ይገኛሉ። ለዚህ ሁሉ አፍራሽ ተግባር የሚያገለግል የሚድያና የአሉባልታ መዋቅርም አደራጅቷል። የኢርትራን ሁኔታ ከዛሬ ነገ ይቀየራል በሚል ተስፋ አግልለውት የቆዩት የአውሮጳ ህብረት ባለስልጣናትም አሁን በስደተኛው ቁጥር ሰግተውና በየመን የነሱን ወዳጅ አገራት ጥቅም ለማስከበር ያሳየውን ዝግጁነትና ተሳትፎ ለማበረታት የገንዘብና የፕሮፖጋንዳ ድጎማ እየሰጡት ነው። የኢትዮጵያ መንግስት በየመን ፖለቲካ የነበረውን ተሳትፎ ችላ በማለቱ የአስመራው መንግስት አዝመራ እያፈሰበት ነው። የሳውዲ ኪንግደምና ኤሜሬትስ፣ ቀደም ሲል ከአስመራ ጋር በወዳጅነት ከቆየችው ኳታር ጋር ተቀላቅለው ስርአቱን እየደገፉት ይገኛሉ። ኤሜሬትስና ሳውዲ የባብል መንደብ ወሸመጥ ላይ ያላቸውን ቁጥጥር የሚያሰፉ የአሰብ ባህር ዳርቻና ባህር ተከራይተው የመን ላይ፣ ኤርትራ ላይና የቀይባህር አካባቢን በተጽኗቸው ስር የሚያደርጉበትን ሁኔታ አመቻችተዋል። ዓረቦችና ሌሎች አገሮች የቀይባህርን አገሮች በተጽኗቸው ስር ባስገቡት ቁጥር የኢትዮጵያ ግዛት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ተጽኖም ባህር አልባ እየሆነ ይሄዳል።

የአስመራው ስርዓትም ከረዥም ጊዜ መገለል በኋላ የማንሰራራት ስሜት ተስምቶታል።ሰሙኑን እንኳን የኳታሩ አሚርና የጀርመን ከፍተኛ ባለስልጣን ከፕረዚዳንት ኢሳያስ ጋር አስመራ ድረስ ሄደው ተወያይቷል። አቶ ኢሳያስም በጥቂት ወራት ውስጥ ለ፪ኛ ጊዜ ሳውዲ ሄደዋል። ቀደም ሲልም አስመራ ውስጥ ያሉት የአሜሪካ ዲፕሎማት የወርቅ ማእድን ማውጫና በኤርትራ ወጣቶች ላይ የባርነት ያህል ብዝበዛ ያካሂዳል የተባለውን የቢሻን ሳይት ጎብኝተው ስርዓቱን የሚያሞካሽ ምስክርነት ሲሰጡ ተደምጠዋል። ትላልቅ የምዕራብና የምስራቅ አገራት ለኤርትራ መንግስት ወዳጅነትና የትብብር መንፈስ ባሳዩ ቁጥር ጅቡቲይም ሱዳንም በኤርትራ መንግስት ላይ ያላቸውን አቋም ለማለዘብ ማሰባቸው የማይቀር ነው። የኤርትራ ተቀዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖሩና ይብዛም ይነስ በኢትዮጵያ መንግስት እየተረዱ፣ ለዛውም ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ኤርትራውያን ያሉባትን፣ ከኤርትራ ጋር ቀጥታ የምትዋሰኗን ኢትዮጵያን ተተው ተሰብስበው ለመምከር የመረጡት ቦታ ኬንያ ናይሮቢ ሆኗል።

ይህ ሁሉ ምን ጂኦፖለቲካዊ አንድምታ እንዳለው ግልጽ ነው። የኤርትራ መንግስት የማተራመስ አጀንዳውን ሳይለቅ የኢጋድ በር ማንኳኳቱና የአቶ ኢሳያስ ፖለቲካዊ ተክለሰውነት ሌላ መልክ መያዙ የቅርብ ጊዜ ጉዳይ ይሆናል ማለት ነው። በዚያው ልክም አቶ ኢሳያስ ስር የተጠለሉት ቡድኖች አፍራሽ ተግባራቸውና አሉታዊ ድምጻቸውን ይዘው ኢትዮጵያን ማወካቸው፣ የኢትዮጵያም ስራ ልማትና ትንሳኤ መሆኑ ቀርቶ እነዚህን መሰል የቅርብና የሩቅ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ወደ መከላከል ለመግባት ስትገደድ ዋናውን ከድህነት የመውጣትና ታሪኳን የማደስ ተልእኮ

ይስተጓጎላል። በኤርትራ ላይ ወሳኝና የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያረጋግጥ አጀንዳ መቀረጽ የሚኖርበትም በዚህ ምክንያት ነው። ኤርትራ ስትራተጂክ አገራዊ ጥቅምና ከዋና ዋናዎቹ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ አጀንዳዎች አንዱ እንጂ ተራ የሴኩሪቲ ጉዳይ ብቻ ተደርጎ መታየም የለበትም።

ኤርትራ ለራሷ ዜጎች ሲኦል ናት። በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ኤርትራውያን ኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛሉ። ብዙዎች ወጣቶች ናቸው። አብዛኛዎቹ የሚሊቴሪና የፕለቲካ ልምድ ያላቸው እንደሆኑ ይታወቃል። ከተቃዋሚ ድርጅቶቹም አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያ የሚገኙና ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በትብብር ለመስራት ችግር የሌለባቸው ናቸው። እነዚህን በቂ አቅም፣ አደረጃጀትና ሎጂስትክስ መድቦ እንዲሁም ወሳኝ የኢንተሊጀንስ ድጋፍ በመስጠት የለውጡ አንቀሳቃሾች ማድረግና ብዙ ውጤት ሊገኝበት የሚችል ስራ መስራት ይችላል። የተወሰነ ለውጥና ቁርጠኝነት ከታየ ደግሞ ተስፋ የቆረጡት ኤርትራውያን፣ እንዲሁም ለውጡን የሚደግፍት የውጭ መንግስታት በአማራጭ ተስፋ እጦት ተመልሰው ከኢሳያስ ጋር ከመተባበርና ዝምታን ከመምረጥ የንቅስቃሴውን አካል የሚሆኑበት ዕድል ይሰፋል። በዚህም ብዙ ችግሮችን መፍታትና ማስወገድ ይቻላል። ኢትዮጵያ በዚህ ዓይነት ፖሊሲ ራሷን ብቻ ሳይሆን አካባቢውን፣ አካባቢውን ብቻ ሳይሆን እየጠፋ ያለው የኤርትራ ህዝብ በተለይም ደገኛውን መታደግ ትችላለች። ይህ ሁሉ ቅዱስ ዓላማ ነው። እንደ አገር ደግሞ ከዚህ በላይ አንገብጋቢ የልማት፣ የደህንነትና የዘላቂ አገራዊ ጥቅም ማስከበርያ ሥራ አይኖርም። መንግስት ለዚህ ተግባርና ስራ የፖሊሲ አቅጣጫ መለየት አለበት። ይህንንም ኃላፊነት የሚወስድን ወደ ትገባር የሚቀይር የተጠናከረ ግብረ ኃይል ማደራጀት አለበት።